# የማንረሳውን በደል ሊያስታውሱን የሚሹት የማንረሳቸው በደለኞች ናቸው

**ከታቱ ተመስገን** (tatu.temesegen251@gmail.com)

በዚህ ርዕስ እንድጽፍ ያነሳሳኝ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች፣ የተወሰኑ እውነታውን ያላገናዘቡ በኢትዮጵያ ላይ የሚያተኩሩ የውጭ ሚዲያዎችና ጥቂት የአገራችን የግል ጋዜጦች ወይዘሪት ብርቱኳን ሚዴቅሳን አስመልክተው እንደ አዲስ የጀመሩት ዘመቻ ነው፡፡

አሁን አሁን የተያዘው አዲስ ፈሊጥ ካሁን ቀደም ተሞክሮ እንደጉም በኖ ከቀረው ዘመቻ የተለየ መልክ ይዞ መቅረቡ አንድ ነገር ሆኖ ሳለ በይዘት ግን ተመሳሳይነት እንዳለው ተረድቻለሁ፡፡ ካሁን ቀደም ወይዘሪቷን አስመልክቶ ይናፈስ የነበረው ዘመቻ ግለሰቧ ምንም አላጠፉም፣ ይቅርታም አልጠየቁም የሚል ነበር፡፡ የአሁኑ ፈሊጥ ደግሞ ግለሰቧ ጥፋተኛ ነበሩ፣ ይቅርታ አግኝተውም ተለቀው ነበር፣ ይቅርታ መጠየቃቸውን የካዱበት አጋጣሚ ሳይኖር የፖለቲካ ሕይወታቸውን ለማጨለም ሲባል የታሠሩ "የህሊና እስረኛ" ሆነዋል ወደሚል እየተቀየረ ነው፡፡ ይህንኑ አዲስ ዜማ ከወደ ባህር ማዶ የሚያቀነቅኑ ጥቂት ሰዎችም ተደምጠዋል፡፡

የሞተን ጉዳይ አንስተው ነፍስ ሊዘሩበት የወር ተረኛ ሆነው ብቅ ካሉት መካከልም ምንነታቸው ገና በወጉ ያልተጣራ ሁለት ቡድኖች አጋጥመውኛል፡፡ አንደኛው መቀመጫውን በቫንኩቨር /ካናዳ/ ማድረጉን የሚገልጸውና ራሱን "ብርቱኳንና ሁሉም የህሊና እስረኞች ይፈቱ ግብረ ኃይል" ብሎ የሚጠራው ቡድን ነው፡፡ ሌላኛው ደግሞ መቀመጫውን በአትላንታ መሆኑን የገለጸው “ነፃነት ለብርቱኳንና ለሁሉም የህሊና እስረኞች አቀናባሪ" እባላለሁ ያለ ቡድን ነው፡፡ ተመሳሳይ ስምና ዓላማ ያላቸው ሁለቱ ቡድኖች ምን እንደሆኑ ለጊዜው በውል ማወቅ ባለመቻሌ እነሱን እንወክላለን የሚሉ ሁለት ግለሰቦች በአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ /ቪኦኤ/ በሰጡት መግለጫ ላይ አተኩራለሁ፡፡

የቡድኖቹ ተወካዮች ለአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ የአማርኛ ቋንቋ አገልግሎት ጥር 8 ቀን 2002 ዓም እንደገለጹት "የሲቪክ ማህበር" አባላት እንደሆኑና "ከዚህ ውጪ የፖለቲካ ዓላማ እንደሌላቸው" ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡ "ኢትዮጵያ ካለችበት ቀውስ ውስጥ መውጣት የምትችለው እንደእነ ብርቱኳንና እሷን የመሳሰሉ የህሊና እስረኞች ሲፈቱና በዴሞክራሲ ሂደት ውስጥ ሲካፈሉ ነው" ብለው እንደሚያምኑ በመግለፃቸው ወዲያው ከፖለቲካው እንዳልራቁ በራሳቸው አንደበት መስክረውልናል፡፡

በቅድሚያ ሁለቱ ግለሰቦች ስለየትኛዋ ኢትዮጵያ እንደሚያወሩ ያወቁም አይመስሉም፡፡ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ለምንኖር ሕዝቦች ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ ኢትዮጵያ ቀውስ ውስጥ የገባች መሆኗን፣ ለዚህም ምክንያት የሆነው ወይዘሪት ብርቱኳንና ለእኛ ግልጽ ያልሆኑ ሌሎች በመታሰራቸው መሆኑን መግለፃቸው ሕዝቡ ይታዘበናል ብለው እንኳን እንዳልገመቱ ጠቋሚ ነው፡፡ ወይዘሪት ብርቱኳንን

ለእስር ያበቃቸው የሕግ የበላይነት መከበር ጉዳይ እንደሆነና ይህም ኢትዮጵያን ወደቀውስ እንዳትገባ ለመከላከል በተደረገ ጥረት እንደሆነ እንዴት መዘንጋት ይቻላቸዋል?

ግለሰቦቹ የ "ሲቪክ ማኀበር አባላት ነን፣ ሌላም የፖለቲካ ዓላማ የለንም" ይበሉ እንጂ የሚሉትና የሚሰሩት ሁሉ እየመሰከረባቸው መሆኑን የተረዱት አይመስልም፡፡ እኔን የሚያሳስበኝ የፖለቲካ አጀንዳ መያዛቸውም አይደለም፡፡ ይልቁንም የሚያሳስበኝ  የሞተውን የወይዘሪት ብርቱኳንን ጉዳይ አስታክከው የያዙት ሌላ አላማና ለማራገብ የመረጡበት ጊዜ  ነው፡፡ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫ ለማካሄድ ጥቂት ወራት በቀሩበት ጊዜ በወይዘሪት ብርቱኳን አስታክከው ሌላ አላማ ሊማራመድ መሞከራቸው ከቀናነት በመነጨ ስሜት እንዳልሆነ ይሰማኛል፡፡

በሌላ በኩል እነዚሁ ግለሰቦች በሰጡዋቸው መግለጫዎች በአንድ በኩል ወይዘሪት ብርቱኳን "መለቀቅ አለባት" በሌላ በኩል "መታሰሯ ጠቅሞናል፣ እኛንም እንድንቀሳቀስ ረድቶናል" የሚል አቋም ከአንድ የሲቪክ ማኀበረሰብ መደመጡ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡  "ኢትዮጵያ ከቀውስ ልትላቀቅ የምትችለው ብርቱኳን ስትፈታ ነው" የሚል አቋም የሚያራምድ በአብዛኛው የፖለቲካ ፓርቲ እንጂ የሲቪክ ማኀበረሰብ አይመስለኝም፡፡ እርግጥ የወይዘሪት ብርቱኳን አፈ ቀላጤ መስለው ላለመቅረብ ሲሉ የጦር መሣሪያ ይዘው ተገኝተዋል ተብለው በቁጥጥር ሥር የዋሉ የእነ ኦነግ ታጣቂዎችን ሳይቀር የህሊና እስረኞች እንደሆኑ በመግለጽ እንዲፈቱም ጠይቀዋል፡፡ ብርቱካንና የታሰሩ ታጣቂዎችን በአንድ ፈርጀው ሁሉንም ይፈቱ ማለታቸው በአንድ በኩል ትክክል ይመስሉኛል፡፡ ሁሉም ህግን በመጣሳቸው፡፡ ትልቁ የሳቱት ግን ህግን የጣሱ ሰዎች የህሊና እስረኞች ሊባሉ አይችሉም፡፡ ኦነግ እንኳዋን የታሰሩበት አባላቱን የህሊና እስረኛ ሲል ተደምጦ አያቅም፡፡

እንግዲህ ወደ ዋናው ጉዳይ ስንሄድ እውነት ወይዘሪት ብርቱኳን የህሊና እስረኛ ናቸውን? የሚለውን ጥያቄ ለመመልከት እንሞክር፡፡ "የህሊና እስረኛ" (Prisoner of Conscience ወይም  በምህፃረ ቃል /POC/ የሚለውን ሐረግ በመፍጠር ለዓለማችን ያበረከተው "አምነስቲ ኢንተርናሽናል" ነው፡፡ ይህንን ሐረግ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት ሜይ 28 ቀን 1961 ባወጣው አንድ ጽሑፍ ነው፡፡

ይኸው ቡድን ከዚያን ጊዜ አንስቶ ለሐረጉ የሰጠውና ከዚያም በኋላ በዓለም አቀፉ ማኀበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው ጽንሰ ሃሳብ የሚያመለክተው "በዘር፣ በሐይማኖት፣ በቀለም፣ በቋንቋ፣ በፆታዊ አቋም፣ በእምነት /የፖለቲካ አመለካከትን ጨምሮ/ ወይም በአኗኗር ዘይቤ ምክንያት ለእስር የተዳረገን ግለሰብ ነው፡፡ ሆኖም አመጽ የሚቀሰቅስ ግለሰብን አያካትትም፡፡"

ከዚህ ጽንሰ ሐሳብ በመነሳት ወይዘሪት ብርቱኳን በፊትም ይሁን በኋላ ለእስር ተዳርገው የነበሩት እውን በሚያራምዱት የፖለቲካ አቋም የተነሳ ነበር ወይ? ፈጽሞ አልነበረም፣ አይደለምም፡፡ እንደሚታወቀው ምርጫ 97ን ተከትሎ በአገሪቱ ተከስቶ የነበረውን አመጽ በመምራታቸውና በማስተባበራቸው ነበር፡፡

በወቅቱ በዚሁ ወንጀል ተከስሰውና ታስረው የነበሩትም ወይዘሪት ብርቱኳን ብቻ አልነበሩም፡፡ እሳቸውን ጨምሮ 38 የቀድሞ የቅንጅት አመራር አባላት በዕድሜ ልክ እስራት እንዲቀጡ ሐምሌ 9 ቀን 1999 ዓም በፍርድ ቤት ተወስኖባቸው ነበር፡፡ እስራቱ የተፈረደባቸው ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች በልዩ አንክሮ በተከታተሉት የፍርድ ሂደት ሲሆን ተከሳሾቹም በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡባቸውን ጠንካራ የቃል፣ የቪዲዮና የዓይን ምስክሮች ማስረጃዎች ማስተባበል ባለመቻላቸው ነበር፡፡

ያም ሆኖ እነወይዘሪት ብርቱኳን ጥፋታቸውን አምነው፣ በድርጊታቸው መፀፀታቸውን ገልፀው ይቅርታ እንዲደረግላቸው መንግሥትን ጠይቀው የነበረው ገና ከፍርድ ውሣኔው በፊት ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በላኩት ደብዳቤ ነበር፡፡ ጥያቄያቸው የፍርድ ውሣኔውን መጠበቅ እንደነበረበትና መጠየቅም ያለባቸው የይቅርታ ቦርዱን መሆኑ ተነግሯቸው ነው ከዚያ በኋላ ይቅርታውን የጠየቁትና በኋላም ተቀባይነትን ያገኙት፡፡

እነወይዘሪት ብርቱኳን ይቅርታ የጠየቁበት ማመልከቻ በይፋ ሕዝብ እንዲያየው ተደርጓል፡፡ ጽሑፋቸው፣ ፊርማቸውና ስማቸው በቴሌቪዥን ለሕዝብ እይታ ቀርቧል፣ በንባብም ተደምጧል፡፡ መልዕክቱም በጣም ግልጽ ነበር፡፡ ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሃይል ለመናድ ተንቀሳቅሰናል፤ መርተናል፤ አስተባብረናል፤ በዚህ አድራጎታችን ሕዝቡንና መንግሥቱን በድለናል፤ አሁን ግን ተፀፅተናልና ይቅርታ ይደረግልን የሚል ነበር፡፡

የፍርድ ውሣኔውና የይቅርታ ጥያቄው ከተመረመረ በኋላ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ይቅርታ ስለተደረገላቸው ነበር ከእስር የወጡት፡፡ እንግዲህ ባገኙት ይቅርታ ተጠቅመው አብዛኞቹ የቅንጅት አመራሮች የገቡትን ቃል አክብረው በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ሲገኙ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በውጭ አገር ሆነው መንግሥትን ለመጣል የትጥቅ ትግል መጀመራቸውን በይፋ አሳውቀዋል፣ ወይዘሪት ብርቱኳን ይቅርታ አልጠየቅሁም በሚል አቋማቸው "ለምነው" ወደነበሩበት እስር ቤት እንዲመለሱ ተደርገዋል፡፡

በተለይም በስዊድን አገር ለደጋፊዎቻቸው ባደረጉት ንግግር "የተለቀቅሁት በእናንተ በደጋፊዎቼና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ግፊት እንጂ ይቅርታ ጠይቄ አይደለም" ሲሉ ድምፃቸውን ብቻ ሳይሆን ምስላቸውንና የታዳሚዎቻቸውን የአዳራሽ ውስጥ ነውጥ ጭምር ቀርፆ በሚያስቀር የቪዲዮ ካሜራ ፊት ለፊት ቆመው ያደረጉት እብሪት የተመላበት ንግግር የመንግሥትን ትእግስት ፍፁም የሚፈታተን ነበር፡፡

ይሁንና መንግሥት ግን በእብሪታቸው ተገፋፍቶ ወዲያውኑ እርምጃ አልወሰደም። ያንን ማድረጉ የሚያስመሰግነው ተግባር ነበር እላለሁ፡፡ ሆኖም ሁኔታው በዝምታ መታለፍ እንደሌለበት ይታመንበት ነበርና ክብርት ሆይ! ያደረጉትን ንግግር ሰምተነዋል፤ መልካምም አልነበረም፡፡ በቀጥታ ዘብጥያ ሊያስወርድዎት እንደሚችል እንደ ሕግ ባለሙያነትዎ ከማንም በላይ ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ይህ ይጠፋዎታል ተብሎም አይታሰብም፡፡ በስዊድን አገር ደጋፊዎችዎን ሰብስበው የተናገሩት ስህተት

ስለመሆኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በግልጽ ያሳውቁ ነበር የተባሉት፡፡ ወይዘሪት ብርቱኳን ግና አስቀድመው ተዘጋጅተውበት ስለነበር የቀለም አብዮት ለመቀስቀስ ይበጀኛል በሚል ለደጋፊዎቻቸው አስበውበት የገለጹትን ይህን አቋም ለመለወጥ ሳይፈልጉ ቀሩ፡፡ በእብሪታቸው እንደፀኑ የተለቀቁት ይቅርታ አግኝተው ሳይሆን በደጋፊዎቻቸው ብርቱ ትግል መሆኑን በመኩራራት አስረግጠው ተናገሩ፡፡ አልቀረላቸውም ህጉ በሚያስገድደው መሰረት ወደዚያው ወረዱ፡፡

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ የሲቪል ማኅበረሰብ ተወካዮች ነን ባይ የወር ተረኞች ደግሞ "ወይዘሪት ብርቱኳን ሚዴቅሳ በማናቸውም ጊዜ ይቅርታ አልጠየቅሁም አላለችም" ሲሉን የቱ ጋ እንዳሉዋቸው ግን አልነገሩንም፡፡ ወይዘሪት ብርቱኳን ራሳቸው ይቅርታ አለመጠየቃቸውን ሲናገሩ ከዓይን ወዲያ ቀላጤ እንዲሉ ይቅርታ ጠይቀዋል ባይ ሆነው መምጣታቸው አስገራሚ ነው፡፡

ወይዘሪቷ ይቅርታ ብለው ነበር የሚሉት ከእስር እንዲለቀቁ በማመልከቻ ጠይቀው የነበረውን ከሆነ ይሄማ ሁላችንንም ያስማማናል፡፡ ከዚያ ወዲህ ግን ይቅርታ መጠየቃቸውን የገለጹበት አንድም አጋጣሚ ስለሌለ ፍፁም ሀሰት ነው። ይልቁንም "ይቅርታ ጠይቀው ነበር" የምትለው ዓረፍተ ነገር ከሰዎቹ አንደበት የወጣችው በከባድ ወንጀል ከባድ ቅጣት የተፈረደባቸውን ግለሰብ የህሊና እስረኛ አስመስሎ ለማቅረብ ስለፈለጉ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ግለሰቧ የህሊና እስረኛ ናቸው ብሎ የሚቀበል ህሊና ግን ራሱ ጤነኛ ሊሆን አይችልም - ያጠራጥራል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ወይዘሪት ብርቱኳን ቀድሞውኑ ለእስር ዳርጓቸው የነበረውን የወንጀል ክስ መከላከል ያልቻሉ እንደነበሩ ይታወሳል፡፡ በፈጸምኩት ድርጊት ተጸጽቻለሁና ይቅርታ ይደረግልኝ ሲሉ ራሳቸው ባቀረቡት ማመልከቻም ላይ ህግ መጣሳቸውን አምነው እንደነበር ማንም ሊክደው አይቻለውም፡፡

ወይዘሪት ብርቱኳን ይቅርታ ተፈቅዶላቸው የነበረውም ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ወሳኝ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው ሊንቀሳቀሱ ቃል በመግባታቸው እንደነበር ይታወቃል፡፡ ከተለቀቁ በኋላ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገልጹ የነበረው አቋማቸው ግን ከዚህ ቀደም ሲጠቀሙበት የነበረውን የቀለም አብዮት ቴክኒክ ለመድገም መወሰናቸውን ነበር፡፡

ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ "እነሱ እኮ ልጆች ናቸው፣ ይጫወቱ በጊዜያቸው" ተብለው በዋዛ ፈዛዛ እንዲታለፉ መጠየቅ አግባብ ነውን? ይህንን ማሰቡ በራሱ ጤነኛነት አይደለም፡፡ ለምን ቢሉ የብዙ ውድ ንጹሃን ኢትዮጵያውያን ደም የፈሰሰበትንና ብዙ የሕዝብና የመንግሥት ንብረት የወደመበትን የ97ቱን አመጽ እንደ ልጆች ጨዋታ ማየት ነው የሚሆነው፡፡

ይህም ብቻ አይደለም። በእውነቱ በአንድ አገር የተረጋጋ መንግሥት አለ የሚባለው የሕግ የበላይነት ሲከበርና ሁሉም ዜጋ በሕግ ፊት እኩል መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ወይዘሪት ብርቱኳን ተከታዮች ስላላቸው ቢያጠፉም፣ ሕግን ቢጥሱም እንዳሻቸው እንዲሆኑና በሕግ ከመጠየቅ እንዲድኑ ለማድረግ መላው ኢትዮጵያውያን ከሚተዳደሩበት የአገሪቱ ሕግ የተለየ ሌላ ሕግ ማውጣትን

ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ አሁን ባለችው ኢትዮጵያ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው፡፡ የአገራችን ሕግ በሁሉም ዜጎች ላይ ተፈፃሚነት ያለው እንጂ የፖለቲካ ደጋፊ ያለውን ዜጋ በልዩነት የሚያስተናግድ አይደለም፡፡

ይህንን ጉዳይ ወይዘሪት ብርቱኳንን አጀንዳ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ጭምር ጠንቅቀው ይረዱታል። ይህን እያወቁ ለምን እንደማያውቁ ሆነው ከተፍ አሉ ከተባለ ጉዳዩ ሌላ ነው፡፡ ምርጫው እየተቃረበ ስለሆነ ሌላ አመጽ፣ ሌላ ብጥብጥ ለመቀስቀስ አስበው እንደሆነ ነው ለመረዳት የቻልኩት፡፡ ለዚህም ነው በርዕሴ "የማንረሳውን በደል ሊያስታውሱን የሚሹት የማንረሳቸው በደለኞች ናቸው" ብዬ ያልኩት፡፡

በማንም ይሁን በማን ያለፈውን ዓይነት አመጽ በዚህኛውም ምርጫ ለመድገም የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ ከወቅቱ የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በሁለት ምክንያቶች የሚያስኬድ አይሆንም ብዬ አስባለሁ፡፡ በአንድ በኩል ሕዝቡ የ97ቱ ድህረ-ምርጫ ብጥብጥ እንዲደገም አለመፈለጉን በማያወላዳ ሁኔታ በተግባር እየገለፀ ይገኛል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አቋቁመውና የተሻለ አሠራር ዘርግተው ለሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በጋራ እየተንቀሳቀሱ መሆኑንም ልብ ይሏል፡፡

በሌላ በኩል መንግሥት የሕግ የበላይነትን በማስከበር በኩል ካለፈው በተሻለ ደረጃ ዝግጅት ያደረገ መሆኑን መገመት አያዳግትም፡፡ መንግሥት በ97ቱ አስቸጋሪ ሁኔታ ከውስጥና ከውጪ በኩል ይደርስበት የነበረውን መጠነ-ሰፊ ጫና ተቋቁሞ ለሕግ የበላይነት መከበር ያሳየውን የማይናወጥ አቋም የሚዘነጋ ሰው ካለ በርግጥም ሰውዬው ጤነኛ ነው ለማለት ያዳግታል፡፡

በመጨረሻም ለመግለጽ የምፈልገው መንግሥት የተገኘውን ሰላምና መረጋጋት እንዲቀጥል ማስቻል በሕዝብ የተጣለበት ከባድ አደራ መሆኑንም ሁሌም መገንዘብ ያሻል።